# የቶምቦላ ወይም ራፍል ዝግጅት ፈቃድ መመሪያን ለማሻሻል የወጣ መመሪያ

## ቁጥር 139/2013

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን

ጥቅምት 2005 ዓ.ም

አዲስ አበባ

## *የቶምቦላ ወይም ራፍል ዝግጅት ፈቃድ መመሪያን ለማሻሻል የወጣ መመሪያ*
## *ቁጥር* **139/2013**

የብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደርን እንደገና ለማቋቋም በወጣው ደንብ ቁጥር 160/2001 መሠረት የሎተሪ ሥራን የማካሄድ ፣ የማስተዳደርና የመቆጣጠር እንዲሁም በሕግና በስርዓት እንዲመራ የማድረግ ስልጣን ለአስተዳደሩ የተሰጠው በመሆኑ:: ቀደም ሲል በሥራ ላይ የነበረው መመሪያ ቁጥር 43/2002 የደንበኞችን ፍላጎት መሠረት ባደረገ መልኩ እና አገራችን የደረሰችበትን የቴክኖሎጂ ዕድገት ግምት ውስጥ በማስገባት መሻሻል እንዳለበት በመታመኑ በአስተዳደሩ የእንደገና ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 160/2001 አንቀፅ 21 መሰረት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ደንቡን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ማውጣት እንደሚችል የተገለፀ በመሆኑ ይህንን የተሻሻለ የቶምቦላ ወይም ራፍል ዝግጅት ፈቃድ መመሪያ አውጥቷል፣

### *1.አጭር ርዕስ*

ይህ መመሪያ “የቶምቦላ ወይም የራፍል” ዝግጅት የፈቃድ አሰጣጥን ሁኔ በተመለከተ ለመወሰን በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ተሻሽሎ የወጣ መመሪያ ቁጥር 139/2013” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

### 2. *ትርጓሜ*

በዚህ መመሪያ ውስጥ የተለየ ትርጉም ካልተሰጠው በስተቀር

1. “ባለስልጣን እና ዋና ዳይሬክተር” ማለት ንደቀደም ተከተሉ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን እና የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር ነው::
2. “አስተዳደር” ማለት የብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደር ነው::
3. “የአስተዳደሩ የበላይ ኃላፊ” ማለት የብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደር ዋና ዳይሬክተር እና ም/ዋና ዳይሬክተር ናቸው::
4. “ቶምቦላ ወይም ራፍል” ማለት የሎተሪ ቲኬቶቹ ቅድሚያ ተከ ይ ቁጥር ተሰጥቷቸው የሚ ተሙ ሆነው አሸናፊው በህዝብ ፊት በሚወጣ ዕጣ የሚለይና ሽልማቱ በዓይነት ብቻ የሚሰጥ ሎተሪ ነው::

5. "ፈቃድ" ማለት ዕጣን ወይም ዕድልን መሠረት ያደረገ የቶምቦላ ወይም የራፍል ጨዋ በማካሔድ ከቶምቦላው ወይም ከራፍሉ የተገኘውን የተጣራ ገቢ ሙሉ በሙሉ ህብረተሰቡን ተጠቃሚ ለሚያደርጉ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተግባራት ማለትም ለትምህርት፣ ለጤና፣ ለስፖርት፣ ለመንገድ፣ ለአካባቢ የተለያዩ የልማት ሥራዎችና ለመሳሰሉት ዓላማ ለሚያውል ለማንኛውም ሰው የሚሰጥ ፈቃድ ነው፡፡

6. "የፈቃድ ተጠቃሚ " ማለት የቶምቦላ ወይም የራፍል ዝግጅት በማድረግ የሚያገኘውን ከወጪ ቀሪ ገቢ ሙሉ በሙሉ ህብርተሰቡን ተጠቃሚ ለሚያደርጉ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተግባራት ለማዋል ከሚመለከተው መንግስታዊ አካል ወይም በህግ ህጋዊ ሰውነት ያለው የበጎ አድራጎት ድርጅት ጋር የፕሮጀክት ሰነድ ወይም ውል ተፈራርሞና ህጋዊ አድርጎ የሚያቀርብ ሰው ነው፡፡

7. "ክፍያ" ማለት በአስተዳደሩ የ ንደገና ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 160/2001 አንቀጽ 18 መሠረት የሚፈጸም የፈቃድ ማውጫና በአንቀጽ 19/1 (ሀ) መሠረት ከሎተሪ ትኬት ሽያጭ ሊገኝ ይችላል ተብሎ በታቀደ ጠቅላላ ገቢ ላይ ተሰልቶ የሚፈፀም የ15% የኮሚሽን ክፍያ ነው፡፡

8. "ሰው" ማለት ማናቸውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

3. <u>የፈቃድ ጥያቄ አቀራረብ ሁኔ</u>

1. ማንኛውም ሰው ቶምቦላ ወይም ራፍል ለማዘጋጀት ሲፈልግ የፈቃድ ጥያቄውን ለአስተዳደሩ በጽሑፍ ማቅረብ አለበት፣

2. ፈቃድ ጠያቂው ከሚያቀርበው ማመልከቻ ጋር የሚከተሉትን መረጃዎች ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

ሀ. የፈቃድ ጠያቂውን ሰው ስምና ሙሉ አድራሻ፤

ለ. ራፍሉ ወይም ቶምቦላው የሚዘጋጅበትን ዓላማ ወይም ጉዳይ፤

ሐ. የሚገኘውን የተጣራ ገቢ ሙሉ በሙሉ ሥራ ላይ በማዋል ስለሚከናወነው ማህበራዊ ተግባርና ስለተጠቃሚው የሚገልጽ በህግ ተቀባይነት ያገኘ የውል ሰነድ፣

መ. ለሽልማት የተዘጋጀውን ዕቃ/ንብረት መለያ ስም /ብራንድ/ ፣ዕቃው የተመረተበትን አገር፣ የሽልማቱን ብዛት፣ የ ያንዳንዱን ዕቃ/ንብረት ዋጋ፣ ለገቢ ሰብሳቢ መስሪያ

ቤት ገቢ ሊደረግ የሚገባው ከሽልማቱ ላይ የሚሰበሰብ የገቢ ግብር እና ለሽልማት የተዘጋጁትን ዕቃዎች/ንብረቶች ጠቅላላ ዋጋ፣

ሠ. ለሽልማት የሚቀርቡት ዕቃዎች በግዢ ወይም በስጦታ በሕጋዊ መንገድ የተገኙ ስለመሆናቸው የሚገልጽ ማስረጃ ፣

ረ. ከአንደኛ ዕጣ ስከ መጨረሻው ደረጃ ለሽልማት የተዘጋጀውን ወይም የ ቀደውን ዕቃ/ንብረት ዋጋ መሠረት በማድረግ የሚዘጋጅ የዕጣ ዝርዝር፣

ሰ. ሊሸጡ የ ሰቡት ቲኬቶች መነሻ ና መድረሻ የቁጥሩ ተከ ይነት ንደተጠበቀ ሆኖ ሊሸጥ የታሰበውን የትኬት ብዛት፣

ሸ. የቶምቦላ ወይም የራፍል ቲኬቱ ነጠላ መሸጫ ዋጋ እና ሊሸጡ የታሰቡትን ትኬቶች ብዛትና ጠቅላላ ዋጋ፣

ቀ. የቶምቦላው ወይም የራፍሉ ቲኬት ከመቼ ጀምሮ ስከ መቼ ድረስ ሊሸጥ ንደ ቀደ (ቲኬቱ የሚሸጥበትን ጊዜ)፤

በ. ቲኬቶቹ የሚሸጡበት ክልል እና የትኬቶቹ የሥርጭትና የሽያጭ ስልት ምን እንደሆነ፣

ተ. ስለቶምቦላው ወይም ራፍሉ ለህብረተሰቡ ሊነገር ወይም ሊገለፅ የ ሰበውን የማስ ወቂያ ዓይነት፣

ቸ. የዕጣ አወጣጡ በምንና ንዴት ባለ ሁኔ ንደሚካሄድ እና ዕጣው መቼ፣ የት እና በስንት ሰዓት ንደሚወጣ፤

ኀ. ዕጣው በሚወጣበት ቀንና ሰዓት ሕዝብ በቦ ው ንዲገኝ የሚተላለፈው የጥሪ ማስ ወቂያ በምን ዓይነት መንገድ ንደሚገለጽ፤

ነ. በዕጣ አወጣጥ ሥነ-ሥርዓቱ ላይ የሚገኙ ዳኞች/ ዛቢዎች ዝርዝርና የሚወክሉት ተቋም ወይም የሕብረተሰብ ክፍል፤

ኘ. በዕጣ መክፈያ የጊዜ ገደብ ውስጥ ዕድለኞች ቀርበው ያልወሰዷቸው ወይም ያልተረከቧቸው ዕቃዎች/ንብረቶች አጠቃቀም ምን ንደሚሆን፤

አ. ዕጣው ከወጣ በኋላ ሕዝቡ የወጣውን ዕጣ ለማወቅ የሚችልበት መንገድ ምን እንደሆነ፣

ከ. ከቶምቦላ ወይም ራፍል ዝግጅቱ ከሚገኘው ጠቅላላ ገቢ ውስጥ ምን ያህሉ በመቶኛ ለሽልማት እንደተመደበ የሚያመለክት መግለጫ፣

ኸ. ፈቃድ ጠያቂው የመመሥረቻ ጽሁፍ የመተዳደሪያ ደንብና ከሚመለከተው መንግስታዊ አካል የተሰጠን ወቅታዊ የሆነ የምዝገባ ሰርተፊኬት፣

ወ. የቶምቦላው ወይም ራፍሉ ትኬት የሚታተምበት ማተሚያ ቤት ስም፣አድራሻ፣ ክልል፣ ወረዳ፣ ቀበሌ፣ የቤት ቁጥር ስልክ እና ፖ.ሣ.ቁ፤ እና

ዐ. የቶምቦላ ወይም ራፍል ሎተሪው የአጭር መልዕክት አገልግሎት (SMS) በመጠቀም የሚካሄድ ከሆነ የአጭር መልዕክት አገልግሎት ለሰጠው ድርጅት ቶምቦላ ሎተሪውን እንዲያካሄድ ፈቃድ የተሰጠው ድርጅት የሚከፍለው የአገልግሎት ክፍያ ከጠቅላላ የቶምቦላ ገቢ ላይ ከ10% መብለጥ የለበትም። ይህንኑ ስምምነታቸውን የሚገልጽ የውል ሰነድ ፈቃድ ጠያቂው ከፈቃድ መጠየቂያ ደብዳቤ ጋር ማቅረብ አለበት።

ዘ. ሌሎች ፈቃድ ለማግኘት ይጠቅሙኛል የሚላቸውን ማናቸውንም ተጨማሪ መረጃዎች፣

*4. ፈቃድ ስለሚሰጥበት ሁኔ*

*የቶምቦላ ወይም ራፍል ዝግጅት ፈቃድ ጠያቂዎች ግዴታዎችና ኃላፊነቶች፣*

1. አመልካቹ ያቀረባቸው መረጃዎችና ማስረጃዎች በዚህ መመሪያ አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ 3.1 እና 3.2 የተገለጹት የተሟሉ መሆናቸው ሲረጋገጥ በአስተዳደሩ የሚፈለጉ ክፍያዎች ንዲፈጸሙ ተደርጎ ፈቃዱ ይሰጠዋል፤

2. በቶምቦላው ወይም በራፍል ዝግጅቱ ላይ ለባለ ዕድል ከሚሰጡ ሽልማቶች የአንደኛው እጣ ሽልማት መሬት እና ጥሬ ገንዘብ ሲሆን፣ የጥሬ ገንዘብ ሽልማት መጠኑን በተመለከተ በየበጀት ዓመቱ በአስተዳደሩ ከሚወሰነው መብለጥ የለበትም።

3. በሽልማትነት ለሚቀርቡት ዕቃዎች/ንብረቶች የገቢ ግብርን ጨምሮ የሚመደበው የእጣ ክፍያ መቶኛ ከቶምቦላው ሎተሪ ሽያጭ ሊገኝ ይችላል ተብሎ ከሚገመተው ጠቅላላ ገቢ ላይ ከ10% ያላነሰ ድርሻ ይኖረዋል፤

4. ያንዳንዱ ፈቃድ የሚጸናው /የሚያገለግለው/ በፈቃድ መጠየቂያው ማመልከቻ ተገልጾ ለተዘጋጀው ለአንድ ጊዜ ቶምቦላ ወይም ራፍል ዝግጅት ዕጣ ማውጣት ብቻ ሆኖ

ቶምቦላው ወይም ራፍሉ ፈቃዱ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ከሶስት ወር በላይ ሳይዘገይ ዕጣው መውጣት ይኖርበታል፤

5. የዕጣው አዘጋጅ ዕጣው ከመውጣቱ በፊት የሽልማት ዕቃዎቹን ለሽልማት ዝግጁ ማድረግ ይኖርበታል፤

6. የዕጣ አዘጋጁ ስለ ቶምቦላ ወይም ራፍሉ ዝግጅት፣ ሽልማት ዓይነቶች እና እጣ አወጣጥ ሥነ ሥርዓት ዝርዝር ሁኔታዎች በተለያዩ የመገናኛ ብዙሀን በይፋ ማሳወቅ አለበት፤

7. የቲኬቱን ሽያጭ ወይም ሥርጭት ለሚያካሂዱ አካላት የሚከፈለው የኮሚሽን ክፍያ ከአስተዳደሩ የኮሚሽን ክፍያ መብለጥ የለበትም::

8. የዕጣ አወጣጥ ሥነ ሥርዓቱ በቲኬቱ ላይ በተመለከተው ቀን መፈጸም ይኖርበታል፤

9. ዕጣው በሚወጣበት ጊዜ ያልተሸጡ ትኬቶች ተለይተው ከዕጣው ውጪ መደረግ ያለባቸው ሲሆን እጣው መውጣት ያለበት ከተሸጠው ትኬት ብቻ ይሆናል፤

10. ዕድለኞች ዕጣው ከወጣበት ቀን ጀምሮ ስከ 6 ወር ባለው ጊዜ ውስጥ ሽልማቱን ማግኘት ያለባቸው ሲሆን የዕድለኞቹ ስምም በመገናኛ ብዙሃን መገለፅ ይኖርበታል፤

11. ለዕድለኛ በሚሰጥ የአይነት ሽልማት ላይ የሚፈለግ የገቢ ግብርና የስም ማዛወሪያ ክፍያ በቶምቦላው ወይም ራፍሉ አዘጋጅ የሚሸፈን ሲሆን ዕድለኛዉ ያለምንም ቅድመ ሁኔ የደረሰውን ዕቃ/ንብረት ለማስረከቢያ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ መረከቡን የዕጣ አዘጋጁ ማረጋገጥ አለበት፤

12. ለዕድለኛ በሚሰጥ የዓይነት ሽልማት ላይ የሚፈለግ የገቢ ግብር በባለ ፈቀዱ የሚከፈል ሆኖ ባለዕድሉ ዕቃውን ከተረከበ በኋላ ፈቃዱ የወሰደው ድርጅት የገቢ ግብሩን ለገቢ ሰብሳቢ መስሪያ ቤት ገቢ ያደረገበትን ማስረጃ ማቅረብ ይኖርበታል፤

13. አጠቃላይ እንቅስቃሴው በሂደት ላይ እያለም ሆነ ከተጠናቀቀ በኋላ እንደአስፈላጊነቱ በአስተዳደሩ ኦዲት የሚደረግ ሲሆን ባለፈቃዱ ከትኬት ህትመት፣ ሥርጭት፣ ሽያጭ፣ ዕጣ ክፍያ ወዘተ ጋር የተያያዙ የሂሳብ ሰነዶችን በጥንቃቄ መያዝ አለበት፤

14. በባለፈቃዱ ከቶምቦላው ወይም ከራፍል ዝግጅት የሚገኘውን ገቢ የሚጠራቀምበት ራሱን የቻለ የባንክ ሂሳብ በመክፈት፣ የሂሳቡ ቁጥሩን፣ የባንክ ሂሳቡ የተከፈተው

በማን ስም እንደሆነና ባንኩ የሚገኝበትን ክልል እንዲሁም የባንኩን ሙሉ ስምና አድራሻ መግለጽ አለበት፡፡

15. የዕጣ አወጣጥ ሥነ ሥርዓቱ ዳኞችና ታዛቢዎች ባሉበትና ለተመልካች ግልጽ በሆነ ቦታ እንዲፈፀም ያደርጋል፡፡

16. አጠቃላይ የዕጣ አወጣጥ ሥነ ሥርዓቱን ተከትሎ የተሸጡና ሳይሸጡ ተመላሽ የተደረጉ ትኬቶችን ብዛትና ዋጋ እንዲሁም የወጡ የዕጣ ቁጥሮችን የሚያመለክትና በዳኞች የተፈረመ ቃለ ጉባኤ የመያዝና ኮፒውን ለአስተዳደሩ የማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡

17. ዕጣው ከወጣ በኋላ እንደ ስርጭቱ ሁኔታ በቂ የዕጣ ዝርዝር የያዘ የዕጣ ማውጫ መግለጫ ዕጣው ከወጣበት ማግስት ጀምሮ ሽያጩ ለተከናወነበት አካባቢ በነፃ እንዲታደል ማድረግ አለበት፡፡

18. የዕጣው አሸናፊ ንደቀረበ ወዲያው ሽልማቱ መሰጠት ያለበት ሲሆን ባለዕድሉ ሌሎች ዕድለኞች እስከሚመጡ መጠበቅ የለበትም፡፡

19. ከተሰጠው የቶምቦላ ወይም የራፍል ዝግጅት ፈቃድ ጋር በተያያዘ የሚደረግ ማንኛውም ዓይነት ማሻሻያ ወይም ለውጥ ሲኖር ፈቃድ የተሰጠው ሰው ለአስተዳደሩ ይህንኑ ወዲያውኑ ሪፖርት የማድረግ እና የአስተዳደሩን የጽሁፍ ፈቃድ የማግኘት ግዴታ አለበት፡፡

20. የቶምቦላ ወይም የራፍል ዝግጅት እንዲያካሄድ ከአስተዳደሩ ፈቃድ የተሰጠው ሰው በዝግጅቱ ሂደት ወቅት በሙሉ አስተዳደሩ የሚመድባቸው ኢንስፔክተሮች የቁጥጥርና የክትትል ሥራ ሲያከናውኑ የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

21. ዕጣው ሲወጣ በዕጣ አወጣጡና ሽልማት አሰጣጡ ሥነ ስርዓት ላይ የአስተዳደሩ ተወካይ እንዲገኝ ከ3 /ሶስት/ የሥራ ቀናት በፊት በጽሁፍ ጥሪ የማድረግ፣

22. ከፈቃዱ መጀመር እስከ መጠናቀቅ ድረስ የተደረገውን አጠቃላይ እንቅስቃሴ የሚያመለክት ከዚህ በታች በተገለፀው መሠረት በጹሁፍ ሪፖርት ለአስተዳደሩ ማቅረብ ያለበት ሲሆን፣

ሀ. በመክፈያ የጊዜ ገደብ ውስጥ የታደሉ የሽልማት ዝርዝሮችን ከነዋጋቸው /ከከፍተኛው እስከ ዝቅተኛው ሽልማት ድረስ ያሉትን/፣

ለ. የዕድለኞችን ስም ዝርዝር፣ ሙሉ አድራሻና ክልላዊ ሥርጭታቸውን፣

ሐ. በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ዕድለኞች ቀርበው ያልወሰዷቸውን የሽልማት ዝርዝሮች ከነዋጋቸው ማመልከት አለበት፡፡

23. ለወጪዎችና ለዕጣዎች የተመደበው የገንዘብ መጠን ከተቀነሰ በኋላ ቀሪው በዚህ መመሪያ አንቀፅ 2 ንዑስ አንቀጽ 2.4 እና 2.5 በተገለፀው መሠረት ስለሚኖረው የአፈፃፀም ሁኔታ አመቺ በሆነው መንገድ በማናቸውም ጊዜ አስተዳደሩ በፕሮጀክት ሰነዱ ወይም በውሉ ላይ በተቀመጠው መሠረት እየተፈፀመ ስለመሆኑ ለሚያደርገው ክትትልና ቁጥጥር ተገቢውን ትብብር እና ድጋፍ ያደርጋል፡፡

24. የፈቃድ መጠቀሚያ ጊዜው ያለቀበትን የፈቃድ ወረቀት ለአስተዳደሩ ተመላሽ የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡

25. ከቶምቦላ ወይም ከራፍል ዝግጅቱ የተገኘው ገቢ የሚጠራቀምበትን የባንክ ሂሣብ መዝጋትና ባንኩን መቀየር ሲፈልግ ለአስተዳደሩ የማሳወቅና የአስተዳደሩን ፈቃድ የማግኘት ግዴታ አለበት፡፡

*5. ፈቃድ ስለሚከለከልበት ሁኔ*

አስተዳደሩ የቀረበለት የፈቃድ ጥያቄ በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ 3.1 እና 3.2 ስር በተገለጹት ዝርዝር ማስረጃዎች ተደግፎ የቀረበ ካልሆነ፤

6. *ፈቃድ ስለማገድና ስለመሠረዝ*

የቶምቦላ ወይም የራፍል ዝግጅት እንዲያካሄድ ፈቃድ የተሰጠው ሰው ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ምክንያቶች ፈቃዱ ሊታገድ ወይም ሊሰረዝ ይችላል፡፡

1. ፈቃድ የሚያሳግዱ ሁኔታዎች፣

ሀ. ፈቃድ ወሳጁ በተሰጠው ፈቃድ ከአስተዳደሩ ጋር ከፈጸመው ውል ውጭ ሲሰራ ከተገኘ፣ ይህንኑ እንዲያስተካክል በጹሁፍ ተገልጾለት ለማስተካከል ፈቃደኛ ካልሆነ፣

ለ. የሥራውን አካሄድ በውሉ መሠረት ለመከታተልና ለመቆጣጠር ለተሰማሩ የአስተዳደሩ ኢንስፔክተሮች መረጃ እና ማስረጃ በመስጠት ለመተባበር ፍቃደኛ ካልሆነ፣

ሐ. በስራው ላይ የፍርድ ቤት የእግድ ትዕዛዝ ከቀረበበት ፍ/ቤቱ ተለዋጭ ትዕዛዝ እስከሚሰጥ ድረስ ታግዶ ሊቆይ ይችላል፣

2. ፈቃድ የሚያሠርዙ ሁኔታዎች፣

ሀ. ፈቃድ የተሰጠው ሀሰተኛ ማስረጃ በማቅረብ መሆኑ ከተረጋገጠ፤

ለ. አስተዳደሩ ሳይፈቅድ የተሰጠውን ፈቃድ በማናቸውም መንገድ ለሦስተኛ ወገን አሳልፎ ከሰጠ፤

ሐ. በተሰጠው ፈቃድ መሰረት በማናቸውም ሁኔታ ስራውን ሳይጀምር ሁለት ወር ወይም 60 ቀናት ከቆየ፤

3. የፈቃድ መታገድና መሰረዝ ውጤት

ሀ. ማንኛውም ሰው ፈቃዱ ስለመታገዱ ወይም ስለመሰረዙ ከአስተዳደሩ የፅሁፍ ማስታወቂያ በደረሰው በ15 ቀናት ውስጥ የተሰጠውን ፈቃድ ወዲያውኑ የመመለስ ግዴታ አለበት፡፡

ለ. ፈቃዱ ስለመታገዱ ወይም ስለመሰረዙ ከአስተዳደሩ ማስታወቂያው በደረሰው በ15 ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ለአስተዳደሩ የበላይ ኃላፊ ማቅረብ ይችላል፡፡

## 7. የፈቃድ፣የኮሚሽን፣ የዕጣ ማውጫ ማሽንና የአዳራሽ ክፍያዎች

1. ማንኛውም የቶምቦላ ወይም የራፍል ዝግጅት ፈቃድ ጠያቂ ሰው ለተሰጠው የፈቃድ አገልግሎት የብር 400.00 /አራት መቶ/ ክፍያ ይፈጽማል፡፡

2. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 2.6 በተቀመጠው መሠረት ፈቃድ ጠያቂው ሰው በቅድሚያ የፈቃድ ክፍያ ና ከቶምቦላው ወይም ከራፍል ቲኬት ሽያጭ ሊገኝ ይችላል ተብሎ ከ ቀደው ጠቅላላ ገቢ ላይ የ15% ኮሚሽን ክፍያ ከሚከተሉት የመክፈያ ዘዴዎች በአንዱ መፈፀም አለበት;

ሀ. በሲ.ፒ.ኦ

ለ. በባንክ ድራፍት ወይም

ሐ. ስከ 6 ወር ዋጋ በሚኖረው የባንክ ወይም የኢንሹራንስ የዋስትና ሠነድ /ጋራንቲ/

3. የኮሚሽን ክፍያው የሚፈፀመው በቅድሚያ በታቀደው ጠቅላላ ሽያጭ ላይ ታስቦ ሲሆን ገንዘቡ በአስተዳደሩ ስም በተከፈተ የባንክ ሂሳብ ተቀማጭ እንዲደረግ ተደርጎ ትክክለኛው የሽያጭ መጠን በአስተዳደሩ ሠራተኞች በሚቀርብ ሪፖርት ከታወቀ በኋላ ባለፈቃዱ ተቀማጭ ካደረገው ገንዘብ የሚመለስለት ካለ ታስቦ ተመላሽ ይደረግለታል፡፡

4. ተመላሽ የኮሚሽን ክፍያው የሚሰላው በዕጣው ማውጫ ቀን በቦታው ተገኝቶ የአስተዳደሩ ኢንስፔክሽን ቡድን በሚያቀርበው ሪፖርት መሠረት ላልተሸጡ የሙሉ ጥራዞች ትኬት ብቻ ይሆናል፡፡

5. የቶምቦላ ወይም የራፍል ዕጣው የሚወጣው የአስተዳደሩን አዳራሽ እና የዕጣ ማወጫ ማሽን በመጠቀም ከሆነ ለሚሰጠው አገልግሎት አስተዳደሩ በሚያወጣው የአገልግሎት ዋጋ መሠረት ክፍያ የመፈፀም ግዴታ አለበት፡፡

## 8. ክልከላ

1. ማንኛውም ሰው ከአስተዳደሩ የተሰጠ ፈቃድ ሳይኖረው ማናቸውንም የሎተሪ ሥራ ማካሄድ አይችልም፣
2. ማንኛውም ሰው የሎተሪ ስራ ለማካሄድ የተሰጠውን ፈቃድ ያለአስተዳደሩ ስምምነት ለሌላ ሰው ማስተላለፍ አይችልም፣

## 9. ቅጣት

ማንኛውም ሰው ያለፍቃድ የቶምቦላ ወይም ራፍል ሎተሪ ዝግጅት ካካሄደ የአስተዳደሩን ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 160/2001 መሠረት አድርጎ እንደጥፋቱ አይነት የሚወስነው ቅጣት ተፈፃሚ ይደረግበታል፡፡

10. <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌ</u>

ይህ መመሪያ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት የተሰጡ የቶምቦላ ወይም ራፍል ሎተሪ ፈቃዶች ቀደም ሲል ሲሰራበት በነበረው መመሪያ ይስተናገዳሉ።

11. <u>የተሻረ መመሪያ</u>

ይህ መመሪያ ከመውጣት በፊት ሲሰራበት የቆየው የቶምቦላ ወይም የራፍል ሎተሪ መመሪያ ቁጥር 43/2002 ተሽሯል።

12. <u>የመመሪያው ተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ በማናቸውም መንገድ ለሚዘጋጁ ቶምቦላዎች ወይም ራፍሎች ተፈጻሚ ይሆናል።

13. <u>መመሪያው ሥራ ላይ ስለሚውልበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር ተፈርሞ ከወጣበት ጊዜ አንስቶ በሥራ ላይ ይውላል።

አዲስ አበባ -------------ቀን 2005 ዓ.ም

መላኩ ፈንታ
የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉሙሩክ ባለሥልጣን
ዋና ዳይሬክተር